http://www.freebirtukan.org
619.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

## ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር ላይ በሰጡት አስተያየት ላይ ከብርቱካንና ሁሉም የህሊና እስረኞች ይፈቱ ግብረ ኃይል የተሰጠ መግለጫ !

ታህሳስ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

በዚምባብዌና በኬንያ እንደታየዉ የጥምር መንግስት መመሥረት የሚቻልበት ሁኔታ ሊኖር ይችል እንደሆን በቅርቡ ከጋዜጠኖች ተጠይቀዉ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ሲመልሱ፣ የቀለም አብዮት በኢትዮጵያ እንደማይሰራ በማስረዳት ከምርጫ በኋላ የሚነሳ ማናቸዉም አይነት ሕገ ወጥ እንቅስቃሴ የትም እንደማያደርስና መዘዙ የከፋ እንደሚሆን ለማስጠንቀቅ ሞክረዋል። አንዳንድ የተቃዋሚ መሪዎች፣ አሁንም ካለፈዉ ስህተት እየተማሩ እንዳልሆነና አሁንም ምርጫዉን በመጠቀም አመጽ ለመቀሰቀስ ሃሳብ ሊኖራቸው እንደሚችሉም ያላቸዉን ግምት ሰጥተዋል።

እንደምሳሌም የጠቀሱት ለአንድ አመት ያህል በግፍና በጭካኔ ታስራ በቃሊቲ እሥር ቤት እየተንገላታች ያለችዋን ታላቅ የሕዝብ መሪ ክብርት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለአገር ዉስጥ ጋዜጠኖች በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ዙሪያ የተናገሩት የሚከተለዉን ነበር፥

> *«ወ/ት ብርቱካንን በምሳሌለነት ብንወሰድ ምህረት አልጠየቅንም ብለዉ፣ ሽማግሌ ቢላክ አምባሳደር ቢላክ አልሰማም አልቀይርም፣ በዉጭ ሄጀ የተናገርኩትን አልክድም፣ አልቀይርም ብለዉ ያሉት። ደጋፊዎቻቸዉ በሚፈጥሩት ብጥብጥ ወይም በዉጭ ኃይሎች ጫና በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከእሥር ቤት እወጣለሁ የሚል ጠንካራ አቋም ስለነበራቸዉ ነው። በወቅቱ ግን በተደጋጋሚ ተነግሯቸዋል። ስህተት እንደሆነ። ከገቡ እንደማይወጡ። ስለዚህ ዋናዉ ነገር ሳይገቡ ቢቀሩ ለሁላችንም እንደሚበጅ በተደጋጋሚ ተነግሯቸዋል። ለአንድ ወር ያህል መንግስት ለምኗቸዋል። በቀጥታም በተዘዋዋሪ መንገድም። ለምን ቢባል ማን ነዉ የሚጠቀመዉ ከዚህ። መንግስት የሚያገኘው አምስት ሳንቲም ጥቅም የለዉም።»*

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ለማስፈታት የተቋቋመዉ ግብረ ኃይል፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ ያቀረቡት ክስ አሳዝኝ፣ ዉሸት የተሞላበትና ይናጋሩበት ከነበረዉ ሃሳብ ጋር የማይገናኝ እንደሆነ ለማሳወቅ እንወዳለን።

በመጀመሪያ ደረጃ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሕገ መንግስቱን አክብራ፣ በሕጋዊ መንገድ ከትግል አጋሮቿ ጋር አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን መሥርታ፣ ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ የተንቀሳቀሰች የአንድ ትልቅ የፖለቲካ ፓርቲ ሊቀመንበር ናት። የ“ቀለም አብዮት“ ለማካሄድም

http://www.freebirtukan.org
619.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org

# Free Birtukan and all prisoners of Conscience in Ethiopia

ሆነ ማናቸዉም የባለሥልጣናትን ፍቃድ ያላገኘ ሰላማዊ ሰልፎችም ሆነ ስብሰባዎች ለማድረግ የተንቀሳቀሰችበት ጊዜ የለም። «ፍየል ወዲህ ቅምዝም ወዲያ» እንደሚባለዉ እቺ ታላቅ የሰላምና የፍትህ ታጋይን ጠቅላይ ሚኒስትሩ «አመጽ እንደቀሰቀሱ» ወይንም «አመጽ ለመቀስቀስ እንዳሰቡ» አድርገዉ በማይገናኝ መልኩ ከ"ቀለም አብዮት" አራማጆች ጋራ ማገናኘታቸዉ ለምን እንደሆነ ሊገባን አልቻለም።

ሽምግሌዎችና አምባሳደሮች አማላጅ እንደላኩ በመግለጽ አቶ መለስ ዜናዊ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «በዉጭ የተናገርኩትን አልቀይርም። ምህረት አልጠየኩም ብለዋል» ሲሉ እርሳቸዉና መንግስታቸዉ «አዛኝ» ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ግን »ግትር» እንደሆኑ ለማሳየት ሲሞክሩም ታዝበናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በዚህ ቃለ መጠይቅ ወቅት እንደ አዲስ ነገር፣ አዲስ ዘመንን የመሳሰሉ አገር ቤት የሚታተሙ ጋዜጦችን እንደማያነቡና በፈረንጆች የሚታተመው ዘኢኮኖሚስት የሚባለዉ ማጋዚን ግን እንደማያመልጣቸዉ ገልጸዋል።

ምናልባትም አዲስ ነገርን ወይንም አዲስ አድማስን የማንበብ ልማድ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢኖራቸዉ ኖሮና ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወደ እሥር ቤት ከመወሰዷ አንድ ቀን በፊት «ቃሌ» በተሰኘዉ ጽሁፏ የጻፈችዉን ቢያነቡ ኖሮ ከላይ የተጠቀሰዉን ፍጹም የተሳሳቱ አባባሎች በአደባባይ ላይናገሩ ይችሉ ነበር።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ቃሌ በተሰኘዉ ጽሁፏ ፡

> *«በሽማግሌዎች የእርቅ ማግባቢያ መንፈስ መሰረት በፖለቲካ የተቀሰቀሰዉን ክስ ፖለቲካዊ እልባት ለመስጠት በማሰብ ለእርቅ ሰል ከሌሎች የፓርቲዉ መሪዎች ጋር ተስማማቼ ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ በሽማግሌዎች አማካኝነት ይቅርታ ጠይቄያለሁ። ይህን ብፈልግም ልለዉጠዉ የማልችለዉ ሐቅ ነዉ።»*

ስትል በግለጽ ይቅርታ እንደጠየቀችና የተሰማማችበትን እንዳልካደች በገሃድ አሳዉቃለች። ወ/ት ብርቱካን «ይቅርታ ጠይቂያለሁ» ብላ በአደባባይ ጽፋ፣ አቶ መለስ ዜናዊ ግን «ይቅርታ አልጠየኩም» ብላለች ማለታቸዉ «እሳት አያቅጥለም» የሚል አይነት እራስን የሚያስገምት፣ የድርቅና አባባል ካልሆነ በቀር የአንድ አገር መሪ ነኝ እንዲሁም አህጉርን እወክላለሁ በማለት ከታላላቅ መሪዎች ጋር ፎቶግራፍ ከሚነሳ ግለሰብ የሚጠበቅ አይደለም።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ጓደኞቻቸው የይቅርታውን ሰነድ ከመፈረማቸው በፊት በአገር ሽማግሌዎች በኩል የደረሳቸው የጠቅላይ ሚኒስትሩ መልእክት *«ይህ ሰነድ ከተፈረመ የሥራ አስፈጻሚ ሥልጣኔን ተጠቅሜ ክሱ እንዲቋረጥ አደርጋለሁ»* የሚል ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ግን ቃላቸውን አላከበሩም። የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል ተደርጎ በእሥረኞች ላይ የእድሜ ልክ እሥራት ሊበየንባቸው ችሏል።

*ታዲያ ቃል የጣሰውና ስምምነቱን ያላከበረው ማን ነው? ቃል የተገባውን የጣሰችው፣ ስምምነቷን ያላከበረችው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሳትሆን አቶ መለስ ዜናዊ እራሳችው አይደሉምን?*

ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ያላደረገችውን አደረገች ብለው መክሰስ ሳያንሳቸው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ፈረንጆች ወይም ደጋፊዎቼ ያስፈቱኛል» ብላ እንደተታለለችም ይናገራሉ።

ከሶስት አመታት በፊት ቃሊቲ እሥር ቤት የነበረች ጊዜ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለቀድሞ የአሜሪካ ቻርጅ ዳፌር ቪኪ ሃደልሰን የጻፉችውን አቶ መለስ ዜናዊ ቢያነቡ ኖሮ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በፈረንጆች ላይ ምንም አይነት እምነት እንደሌላትና  በነርሱ ላይ የማትደገፍ መሆኗን ባወቁ ነበር።

ጠቅላይ ሚኒስተሩ በተሳሳተ መንገድ እንዳሉትም፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅስ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ስትገባ ደጋፊዎቼ ያስፈቱኛል በሚል ተስፋም አልነበረም። ወደ ቃሊቲ የገባችው እውነትን ውሸት ፣ ውሸትን እውነት በማለት፣ ክብሯንና ነጻነቷን አሳልፋ ከመስጠት፣  መሞትን ስለመረጠች ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ለስድስት ወራት የአቶ መለስ ዜናዊ መንግስት በነፍሰ ገዳዮች ላይ እንኳን ባልታየ ሁኔታ ለስድስት ወራት በጨለማ ቤት ውስጥ እንድትቀመጥና የስነ ልቦና ቶርቸር ሰለባ እንድትሆን ባደረገ ጊዜና የአገር ሽምግሌዎች በቃሊቲ ሲጎበኟት « ከእሥር ቤት ልውጣ እንጂ መንግስት የሚጠይቀኝ ሁሉ አደርጋለሁ» ብላ ለፍቃዳቸውና ለሽፍጣቸው ተንበርክካ፣ እራሷንና ሕሊናዋን ሽጣ ከቃሊቲ እሥር ቤት በወጣች ነበር።

በዚህ በጋዜጣዊ መግለጫ አቶ መለስ ዜናዊ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከእሥር ቤት እንደማትወጣም በይፋ ገልጸዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን የተናገሩት በዋናነት የተቃዋሚውን እንቅስቃሴ ተስፋ ለማስቀረጥ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ የረሱት ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር እንደማናችንም ስጋ ለባሽ እንደሆኑና የርሳቸው ቃል የእግዚአብሄር ቃል እንዳልሆነ ነው። ወሳኙ እርሳችው ሳይሆኑ ወሳኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሁም  በሰማይ የሚኖረው ታላቁ እግዚአብሄር ነው።

**በመሆኑም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአደባባይ የሚሰጧቸው ከእውነት የራቁ አሳዛኝ መግለጫዎች እራሳቸውንና አገዛዛቸውን ከማስገመትና አገርን ከመጉዳት ውጭ የሚያመጣው ምንም አይነት ጥቅም እንደሌለ ተረድተው ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እንዲፈቱ እንጠይቃለን። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በማሰር የሚገኝ አንዳች የፖለቲካ ጥቅም ሊኖር**

http://www.freebirtukan.org
619.597.1086
PO Box 3158, Cypress, CA 90630
admin@freebirtukan.org



**አይችለም። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በማሰር ይህ መንግስት ጊዚያዊ ጥቅም ያገኘና ሥልጣኑን ለማራዘም የቻለ ሊመስለዉ ይችላል። ነገር ግን አንዷን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን በማሰሩ በአሥር ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ብርቱካን ሚደቅሳዎችን ነዉ የወለደዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በእሥር ቤት በቀየች ቁጥር የፖለቲካዉ ቀዉስ የበለጠ ከመካረሩም ባሻገር ለሰላምና ለብሄራዊ እርቅ አመቺ ሁኔታ እንዳይፈጠር ያደርጋል።**

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ወንጀለኛ አይደለችም። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሕሊና እሥረኛ ናት። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ከውርደት ክብርን፣ ከባርነት ነጻነትን፣ ከዉሸት እዉነትን፣ ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከአስመሳይነት ሐቀኝነትን የመረጠችና ሌሎች ኢትዮጵያዉያንን አሳልፋ ከመስጠት ይልቅ እራሷን ለሕዝብ ጥቅም አሳልፋ የሰጠች ዳግማዊት ጣይቱ ብጡል ታላቅ የኢትዮጵያ ልጅ ናት።

በአገር ዉስጥና ከአገር ዉጭ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ሁሉ፣ ዘር ጎሳ ኃይማኖት ጾታ እድሜ የፖለቲካ አስተሳሰብ የትምህርት ደረጃ ሳይከፋፍለን ለዜጎች መብት፣ ለወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳና ለሁሉም የሕሊና እሥረኞች መፈታትና ለአንዲት ኢትዮጵያ አንድነትና ደህንነት በጋራ እንድንቆም ጥሪ እናቀርባለን።

"ብርቱካንና ሁሉም የህሊና እስረኞች ይፈቱ" ግብረሀይል